# የፈኩት አበቦች

**መኰንን ኃይሉ** 09-09-14

አበባየሆሽ ለምለም፣

ባልንጀሮቼ ለምለም፣

ቁሙ በተራ ለምለም፣

እንጨት ሰብሬ ለምለም፣

ቤት እስክሰራ ለምለም፤

እንኳን ቤትና ለምለም፣

የለኝም አጥር ለምለም፣

እደጅ አድራለሁ ለምለም፣

ኮከብ ስቆጥር ለምለም፤

አበባ የብር ሙዳይ ኮለል በይ፣

አበባዬ እቴ አበባዬ እቴ…፤

"አበባየሆሽ፣ በኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር አዲስ ዓመት በገባ ቁጥር በወርሃ መስከረም መጀመሪያ ልጃገረዶችና ኮረዶች የሚጫወቱት የተወደደ ባሕላዊ ዜማ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊያን ከሌሎች ሃገር ሕዝቦች ከምንለይባቸው ባህላዊ እሴቶቻችን መካከል የራሳችን የሆነ የዘመን አቆጣጠር እንዲሁም የጽሁፍ ፊደላት ባለቤት መሆናችን ትልቅ ቦታ የሚይዙ ናቸው፡፡

እንግዳ ተቀባይ እንደመሆናችን መጠን በየዓመቱ አዲሱን ዓመት "እንኳን በሠላም መጣህ!!" በማለት "የአበባየሆሽ" ባሕላዊ ዝማሬ በየቀየውና በየመንደሩ መስማት የተለመደ ነው፡፡ አጭር እድሜ ያላትና በ13ኛ ወርነቷ በኢትዮጵያዊያን ዘመን አቆጣጠር ብቻ የምትታወቀው የጳጉሜ ወር በተለይ አበባየሆሽን በናፍቆት ሊሚጠብቁት ኮረዶችና ወጣት ወንዶች ልጆች ረጅም ወር ነች ማለት ይቻላል፡፡

አሮጌው ዘመን በአዲስ በተተካ ጊዜ በልጃገረዶች ከሚዜመው ባሕላዊ የአበባየሆሽ ጨዋታ በተጨማሪ ተፈጥሮም "እንኳን ከዘመን ዘመን አሸጋገራችሁ!!" በሚል መንፈስ ሜዳውና ሸንተረሩን ውብ በሆነው የአደይ አበባ በማስጌጥ ለበዓሉ ልዩ ድምቀት ይሰጠዋል፡፡

ከልጃገረዶች የአበባየሁሽ ዜማ ባሻገር ወንዶች ልጆችም በዚህ አስደሳች ወቅት "እንኳን ከዘመን ወደ ዘመን አሸጋገራችሁ" በሚል መልካም ምኞታቸውን ለመግለጽ ሲያስጌጡት የከረሙትን በወረቀት የተሳለ አበባ በየቤቱ ለማደል ውር…ውር ሲሉ ማየት የተለመደና በዓሉን ይበልጥ የሚያደምቀው ክስተት ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን አበባን ለደስታ፣ ለሐዘን፣ ለመልካም ምኞት መግለጫና ለሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች የምንጠቀም መሆናችን ከሌሎች ሃገር ሕዝቦች ጋር ከሚያመሳስሉን ነገሮች አንደኛው ለመሆኑ አያጠራጥርም፡፡ የሃገራችን አየር ንብረትም ሆነ መልክዓምድር አቀማመጥ እንደ መስቀል ወፍ በዓመት አንድ ጊዜ ብቅ ብሎ ከሚጠፋውና በኢትዮጵያ ብቻ ከሚገኘው የአደይ አበባ በተጨማሪ ጽጌረዳ፣ ካርኔሽን፣ ሐይፐሪከም፣ ጂፕሶፊሊያ እንዲሁም የተለያዩ ቅንጥብና ሌሎች በርካታ የአበባ ዝርያዎች ውበት ደምቀውና አምረው መታየት ከጀመሩ ውሎ አድሯል፡፡

አበባን ለማህበራዊ ጉዳዮች መገለጫ ብቻ የተጠቀምንባቸው ዓመታት ላይመለሱ ለዘላለም አልፈዋል፡፡ አሁን ያለንበት ዘመን ኢትዮጵያ ተወዳጅና እጅግ ተፈላጊ የሆኑ አበባዎችን ለዓለም ገበያ የምታቀርብበት ዘመን ነው፡፡

ሃገሪቱ በአበባና ሌሎች የሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ልማት ዘርፍ ያላትን እምቅ የተፈጥሮ ሃብት እንደጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም የወጪ ንግዱን በማጎልበት ዘርፉ ለኢኮኖሚያው ማደግ አስተዋጽኦ ማድረግ ከጀመረ አሥርት ዓመታት አስቆጥሯል፡፡ የሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ልማት ኢንዱስትሪ ሃገሪቱ የግብርና ምርቶችን ለዓለም ገበያ በማቅረብ የምታገኘውን የውጭ ምንዛሪ በማሳደግ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ የሚገኝ ዘርፍ ነው፡፡

የሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ልማት ዘርፍ ከተጀመረ ጥቂት ዓመታት ቢሆንም ዘርፉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ዕድገት ከማስመዝገቡም በላይ ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድልን መፍጠር ችሏል፡፡ ከዚህም ባሻገር በድህነትና በጦርነት የምትታወቀውን የሃገሪቱን መጥፎ ገጽታ በመለወጥና ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ

መድረኮች ላይ በማስተዋወቅ ኢንዱስትሪው የማይናቅ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ብቻ ኢትዮጵያ ከሆርቲካልቸር ልማት ዘርፍ 245 ሚሊዬን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ማግኘቷን የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ዓለም ወልደገሪማ ይገልጻሉ፡፡ ዘርፉ በአጠቃላይ ካስገኘው ገቢ የአንበሣውን ድርሻ ማለትም 200 ሚሊዬን ዶላር የሚጠጋ የውጭ ምንዛሪ የተገኘው ለዓለም ገበያ ከቀረበው የአበባ ምርት ነው፡፡

ይህ ገቢ ከሪፓትሪዬሽን እና ከሐየር ሊዝ በባንክ በኩል ወደ ሃገሪቱ የገባውን የውጭ ምንዛሪ ያላካተተ ነው፤ ይህ ገቢ ሲካተት በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ በዚህ ዘርፍ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ወደ280 ሚሊዬን ዶላር ያደርሰዋል፡፡

ዘመኑ ኢትዮጵያ ቀድሞ ከነበረችበት አስከፊ ሁኔታ ወጥታ ተወዳጅና ተመራጭ አበባዎችን ለዓለም በገፀ በረከትነት የምታበረክትበት ወቅት በመሆኑ፤ በተጠናቀቀው 2006 በጀት ዓመት ብቻ ሃገሪቱ ከ2 ቢሊየን 386 ሚሊዬን በላይ የአበባ ዘንጎች፣ ከ145 ሺህ ቶን በላይ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም እፀ ጣዕም ምርቶች ለውጭ ገበያ አቅርባለች ማለት ነው፡፡

ኢትዮጵያ አበባን በዋናነት ከምትልክባቸው ሃገራት መካካል ትልቁን ድርሻ የሚይዘው ኔዘርላንድስ ነው፡፡ ኔዘርላንድስ በኢትዮጵያ ከሚመረተው አበባ 83 በመቶ የሚሆነውን የምትገዛ ሃገር ናት፡፡ ጀርመን፣ ኖርዌይ፣ ሣውዲ ዐረቢያ፣ ቤልጂዬም፣ አሜሪካ፣ ጃፓን፣ ሩሲያ፣ ፈረንሣይ፣ ጣሊያንና ዩናይትድ ዐረብ ኢምሬትስ እንደየቅደም ተከተላቸው የገበያ ድርሻ አላቸው፡፡

የሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ኢንዱስትሪ ለገጽታ ግንባታና ለቀጣይ ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት መረጋገጥ ከሚኖረው ሚና ባሻገር 183,000 ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥሯል፡፡ ኢንዱስትሪው ከያዘው አጠቃላይ የሰው ኃይል መካከል ሰባ በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡

የሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ልማት ዘርፍ መንግሥት ሀገሪቱን ከድህነት ለማውጣትና ፈጣን ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማረጋገጥ ተግባራዊ ያደረገው የልማት ፖሊሲ ፍሬዎች መካከል በውጤታማነቱ እንደ አብነት ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡

የሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ልማት በሀገራችን በስፋት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ተከታታይ እድገት ሲያስመዘግብ የቆየ ነው፤ ዘርፉ በጅማሬ ላይ በነበረበት በ1997 በጀት ዓመት የተገኘው የውጭ ምንዛሪ 28 ነጥብ 5 ሚሊዬን ዶላር ነበር፡፡ በዘርፉ እየተመዘገበ ያለው አፈጻፀምም ከዓመት ዓመት ዕድገት በማሳየት ባለፈው በጀት ዓመት 246 ሚሊዬን ዶላር ገቢ ማስገኘት ችሏል፡፡ የዘርፉ ዕድገት በተጠናቀቀው የበጀት ዓመትም ቀጥሏል፤ ገቢው ካለፈው በጀት ዓመት የገቢ አፈጻፀም ጋር ሲነጻጸር ከስድስት በመቶ በላይ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ከ120 በላይ የሚሆኑ የውጭና የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች በዘርፉ ተሰማርተዋል፤ በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ደግሞ ስድስት አዲስ የውጭ ኩባንያዎች ከኢኳዶር፣ ህንድ፣ ኔዘርላንድስ፣ ቤልጂየምና ሌሎች ሀገራት በመምጣት ወደ ሥራ መግባታቸው አሁንም የዘርፉ ዕድገት እንደቀጠለ ለመሆኑ ጥሩ ማሣያ ነው፡፡

ዓለማችን እ.አ.አ በ2008 እና በ2011 በኢኮኖሚያዊ ቀውስ ክፉኛ በተመታችበት ወቅት ኢኮኖሚያዊ ቀውሱ በዓለም ታዋቂና ስመ ጥር የሆኑ የተለያዩ ኩባንያዎችንና ኢንዱስትሪዎችን ከመፈታተኑም ባሻገር አንዳንዶቹንም ለከፋ ኪሳራ መዳረጉ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡

ዓለም ዓቀፉ ምጣኔ ሀብታዊ ቀውስ የአበባን ገበያ በአውሮፓ፣ ሰሜን አሜሪካ፣ መካከለኛው ምሥራቅ፣ እስያና ሌሎች ገዥ ሀገራት እንዲቀዛቀዝ ማድረጉ ይታወሳል፡፡ ይህም ክስተት በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ኢንዱስትሪ ዕድገት ላይ የራሱ የሆነ ጫና የነበረው ለመሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡

ይሁንና በቅርብ ዓመታት (2008 እና በ2011) ለሁለት ጊዜያት የተከሰተውና ጠንካራ ኢኮኖሚ ያላቸውን ሀገራት እንኳን ሳይቀር እጅግ የተፈታተነው ዓለም አቀፉ ምጣኔ ሀብታዊ ቀውስ በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ኢንዱስትሪ ዕድገት ላይ የራሱ የሆነ ጫና የፈጠረ ቢሆንም ዕድገቱን ግን ሊገታው አልቻለም፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ልማት ኢንዱስትሪ ጥንካሬና የመንግሥት የልማት ስትራቴጂና ፖሊሲ ውጤታማ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡

ሀገሪቱ በሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ልማት ዘርፍ ያላት ተሞክሮ ከአንድ አሥርት ዓመታት ባይበልጥም በአጭር ጊዜ አመርቂ ውጤት ተመዝግቧል ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ በአሁኑ ወቅት ሀገሪቱ አበባን ለዓለም ገበያ በማቅረብ በዘርፉ ከ30 ዓመታት በላይ ልምድ ካላት ከኬንያ በመቀጠል ከአፍሪካ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ እንዲሁም የኢንተርናሽናል የንግድ ማዕከል (International Trade Center) ኢትዮጵያ አበባን በተለይም ከት ፍላወር (cut flower) የተባለውን የአበባ ዝርያ ለውጭ ገበያ በማቅረብ በዓለም በአራተኛ ደረጃ ላይ ያስቀምጣታል፡፡ በአንድ ወቅት ቡና "አረንጓዴ ወርቃችን" በመባል የውጭ ምንዛሪ ማስገኛ ብቸኛ አማራጭ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ አሁን ግን የ13 ወራት ፀጋ ባላት ኢትዮጵያ ፈክተውና ደምቀው የሚታዩት አበቦች ልብን ከሚሰርቅ ውበታቸውና ከሚያውደው መልካም መዓዛቸው ባሻገር 'አለንልሽ እማማ' በሚል ስሜት ይመስላል ለኢኮኖሚው ዕድገት አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ የሚገኙት፡፡

በመሆኑም በሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ልማት የታየው እመርታ ይበልጥ እንዲጎለብትና ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አልፋ ተርፋ በዓለም ደረጃ ግንባር ቀደም የአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም እፀ ጣዕም ምርቶች አምራችና ላኪ እንድትሆን በማድረግና በሀገሪቱ የተጀመረውን ድህነትን ታሪክ የማድረግ ራዕይ በማሳካት ረገድ ኢንዱስትሪው የራሱን የታሪክ አሻራ ጥሎ እንዲያልፍ ባለሐብቱ፣ ኤጀንሲውና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተቀራርበውና ተቀናጅተው መሥራታቸው አጠያያቂ አይሆንም፡፡